የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል

ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ

የሆሳዕና ትምህርት ኮሌጅን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የመስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር -/2014 ዓ.ም

የካቲት 2014

የመስተዳደር ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ

የክልሉ የመስተዳደር ምክር ቤት፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የትምህርት ኮሌጆች መተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር-/2014 አንቀጽ 4 እና በክልሉ የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 192/2014 አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡-

1. አጭር ርዕስ፤

ይህ ደንብ "የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሆሳዕና ትምህርት ኮሌጅን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የመስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር - /2014 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ፤

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1) በዚህ ደንብ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሐረጎች ሁሉ በአዋጁ ከተሰጣቸው ትርጓሜ ጋር በተጣጣመ አኳኋን ይተረጎማሉ፤
2) "አዋጅ" ማለት የደቡብ ክልል የትምህርት ኮሌጆችን ለማስተዳደር የወጣው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል አዋጅ ቁጥር -/2014 ነው፤
3) "ደንብ" ማለት የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የትምህርት ኮሌጆችን ለማስተዳደር የወጣውን አዋጅ ቁጥር -/2014 ለማስፈጸም የወጣ የመስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ነው፤
4) "ተቋም" ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኝ የመንግስት የትምህርት ኮሌጅ ነው፡፡

3. ተጠሪነት፤

የትምህርት ኮሌጁ ተጠሪነት ለክልሉ ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

4. መቋቋም፤

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሆሳዕና ትምህርት ኮሌጅ ከዚህ በኋላ (የሆሳዕና ትምህርት ኮሌጅ) እየተባለ የሚጠራ እራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

5. ዋና ግቢ

የትምህርት ኮሌጁ ዋና ግቢ በሆሳዕና ከተማ ሆኖ፣ እንዳስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

6. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሆነ ማንኛውም መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ እንደገና ለተቋቋመው ለሆሳዕና ትምህርት ኮሌጅ ተላልፏል፡፡

7. የተሻሩ ህጎች

1) በደንብ ቁጥር 22/96 በትምህርት ቢሮ ስር ያሉትን የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችን የተመለከተው ድንጋጌ በዚህ ደንብ ተሽሯል፤
2) ማንኛውም ይህን ሕግ የሚቃረን ደንብ፣ መመሪያና የዘልማድ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

8. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

አዋጁንና ይህንን ደንብ ካልተቃረኑ በስተቀር ደንብ ቁጥር 22/96 እና ደንቡን መሰረት አድርገው የወጡ መመሪያዎች በሌላ እስኪተኩ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

9. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በመስተዳደር ምክር ቤት ጸድቆ፣ በደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሀዋሳ

የካቲት 2014 ዓ.ም

እርስቱ ይርዳ

የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት

ርእሰ መስተዳደር